# በሌላ መንግሥት በወንጀል የሚፈለግን ሰው አሳልፎ ስለመስጠት በኢትዮጵያ ሕግ ።

በፍሥሐ ይመር *

## መግቢያ

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ በሌላ መንግሥት በወንጀል የሚፈለግን ሰው አሳልፎ የመስጠት ሥርዓትን በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥ በሚመለከት የተወሰኑ ጠቃሚ ፃጽታዎችን ለመመርመር ነው ። ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው አሳልፎ መስጠትን የሚመለከቱ ውሎችና ስምምነቶችም ሆኑ የሀገር ውስጥ ሕግ በዚሁ ጽሑፍ ውስጥ ይነሳሉ ። ይህም አመለካከት የኢትዮጵያ የሕግ አወቃቀር፣ አሳልፎ መስጠትን በሚመለከት በየጊዜው የሚነሱትን ጥያቄዎች ለመፍታት በቂነቱን ለመወሰንና አሳልፎ መስጠትን በሚመለከት ኢትዮጵያ ያለባትን ዓለምአቀፋዊ ግዴታ ለመረዳት ነው ።

አሳልፎ መስጠት ማለት በወንጀል ተጠያቂ ነው የተባለው ወይም ጥፋተኝነቱ የተወሰነበት ግለሰብ በጊዜው በክልሉ ውስጥ የሚኖርበት መንግሥት ይህንኑ ተጠያቂ ነው የተባለ ወይም የተከሰሰ ግለሰብ በክልሉ ውስጥ ወንጀሉን ፈጽሟል ለተባለበት መንግሥት ፣ ወይም ወንጀለኝነቱን ላረጋገጠው መንግሥት ማስተላለፍ ማለት ነው ። አሳልፎ የመስጠት ዋና ዓላማ የሚያርፈው ወንጀል በዓለም ሕብረተሰብ ላይ እንዳይፈጸም ለመግታት ባለ ምኞት ላይ ነው ። ለዚህም ግብ በጥፋተኝነት ላይ ያለው ወንጀለኛ ፍርዱን ማግኘት ያለበትና ይህንንም ፍርድ መፈጸም የሚገባው ወንጀሉን በፈጸመበት መንግሥት ቦታ መሆኑ ይመረጣል ። ይህም ምርጫ ጥፋተኝነቱን የሰጠውን መንግሥት በሚመለከት ወንጀለኛው ተመልሶ እንዲሰጠው የጠየቀውን መንግሥት የፍትህ አስተዳደር የሚያከብር መሆኑን ፣ እንዲሁም በጥፋተኛው ግለሰብ የተፈጸመውን ተግባር የሚኮንን መሆኑን ይጠቁማል ፤ እንዲያውም ተግባሩ አስቀጭ እንደሆነ ይቆጥረዋል ።

እዚህ ላይ በቅድሚያ መጠቀስ የሚገባው ኢትዮጵያ ሌሎች ብዙ አገሮች እንዳላቸው ዓይነት አሳልፎ መስጠትን በሚመለከት የተሟላ ሕግ የሌላት መሆኑ ነው ። አሳልፎ መስጠትን በሚመለከት ከሱዳን ጋር ካደረገችው ውልና ሌሎች አንድ ወይም ሁለት ድንጋጌዎች ከያዙ ዓለምአቀፍ ስምምነቶች በስተቀር የኢትዮጵያ አሳልፎ የመስጠት ሕግ ወንጀለኛ መቅጫው ሕግ የያዘው ጥቂት ድንጋጌዎችን ብቻ ነው ። በኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በተቋቋመበት አዋጅ 34/1/1974 የታገደው የተሻሻለው ሕገ መንግሥትም እንዲሁ አሳልፎ መስጠትን በሚመለከት የተወሰኑ መሠረተ ሀሳቦችን ይዟል ።

ምንም እንኳ የተሻሻለው ሕገ መንግሥት አሁን በሥራ ላይ ባይሆንም ቢያንስ ከታሪክ አንጻር አሳልፎ የመስጠትን ጥያቄ የሚመለከት ድንጋጌዎቹን ዳጭሩ በመጥቀስ መጀመሩ ጠቃሚ ይሆናል ። በተጨማሪም በዚሁ ሕገ መንግሥት ውስጥ ያሉት አሳልፎ መስጠትን የሚመለከቱ መሠረተ ሀሳቦች ሁለገብ ተፈጻ

---

* ዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሕግ ክፍል ኃላፊ

ሚነት እስካላቸው ድረስ በማንኛውም አመች ሁኔታ ስለአሳልፎ መስጠት ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎች አስፈላጊ ሆነው በሚገኙበት ጊዜ በየትኛውም የወደፊት የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው መሠረተ ሀሳቦች ናቸው ፡፡

በዚሁ ሕገ መንግሥት ውስጥ ስለአሳልፎ መስጠት ሁለት መሠረተ ሀሳቦች ተጠቃለዋል ፡፡ አንደኛው የራስን ዜጋ ለሌላ መንግሥት አሳልፎ አለመስጠት ነው ፡፡ ስለዚህም አንቀጽ 50 « ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለሌላ አገር መንግሥት አሳልፎ አይሰጥም ፡፡ » ይላል ፡፡ የዚህ ድንጋጌ ፍሬ ነገር በግልጽ የሚያሳየው መንግሥት የራሱን ዜጋ ለሌላ አገር አሳልፎ ለመስጠት የሚያስችለው ውል በሕግ መዋዋል እንደማይችል ፣ ወይም አሳልፎ በመስጠት ውል ወይም ስምምነት ኢትዮጵያ ዜጋዋን አሳልፋ ለመስጠት ግዴታ በመግባት የውሉ ወይም የስምምነቱ አባል እንድትሆን ማድረግ እንደማይቻል ነው ፡፡ ከውጤቱ አንጻር ይህም ማለት ተጻራሪ የሆነ የውል ግዴታ ቢኖርም እንኳ አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ለሌላ አገር መንግሥት አሳልፎ አይሰጥም ማለት ነው ፡፡

በአንቀጽ 50 የተጠቃለለው ሁለተኛው መሠረተ ሀሳብ ደግሞ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች ከተደነገገው ውጭ ማንም ሰው አሳልፎ አይሰጥም የሚለው እምነት እጅግ በጣም ትንሽ አገሮች ይቀሩ እንደሁ እንጂ በሁሉም አገሮች ብሔራዊ ሕገ መንግሥቶችና አሳልፎ የመስጠት ሕጎች ውስጥ ተጠቃሎ ይገኛል ፡፡ ይህም የሚጠቁመው አሳልፎ መስጠትን በሚመለከት በውል ላይ የተመሠረቱ ግዴታዎች ከሌሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ጥገኝነት የጠየቁ ወንጀለኞችን አሳልፎ መስጠት እንደማይችል ነው ፡፡ ይህ ደግሞ በኢትዮጵያና በሌላ መንግሥት መካከል አሳልፎ መስጠትን በሚመለከት ውል ከሌለ ፤ ወይም ሌሎች አገሮች ወንጀለኛን አሳልፎ ስለመስጠት ሁኔታ በጋራ የተዋዋሉት ኢትዮጵያ አባል ያልሆነችበት ውል ቢኖርም ከኢትዮጵያ ተመልሶ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበበት በጥገኝነት ላይ ያለ ወንጀለኛ የኢትዮጵያ መንግሥት መልሶ የሚቃጣውን ተግባር ሕጋዊ አይደለም በማለት ለመቃወም መብት እንደሚኖረው የሚያሳይ ነው ለማለት ያስችላል ፡፡ አሳልፎ መስጠት በብዙ አገሮች የመስተዳድሩ ወይም ፖለቲካዊ ተግባር ብቻ አይደለም ፤ ስለሆነም ጥገኝነት የጠየቀው ወንጀለኛ ተመልሶ ይሰጠኝ በሚል ለቀረበለት ጥያቄ በመስማማት መንግሥት የሚሰጠውን ውሳኔ በመደገፍ ወይም በመቃወም የሚሰጡ ብይኖችን የሚያያይዝና የተወሳሰበ የፍርድ ሥርዓትም የሚያቅፍ ነው ፡፡ በፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች ላይ የተመሠረቱ አሳልፎ የመስጠትን ሁኔታ የሚመለከቱ ጉዳዮች በኢትዮጵያ ፍጽሙን የሉም ፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው ባለፉት ብዙ ዓመታት አሳልፎ መስጠትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ሳይኖሩ ቀርተው ሳይሆን ይህ ሁኔታ ያጋጠማቸው ግለሰቦች ምናልባት ጉዳያቸውን ወደ ፍርድ ቤት ባለመውሰዳቸው ወይም ጉዳዩን ፍርድ ቤት ለማቅረብ በሚያመቻቸው ሁኔታ ላይ ሳይሆኑ በመቅረታቸው ምክንያት ሊሆን ይችላል ፡፡

## <u>የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ [1] ፡፡</u>

የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አሳልፎ መስጠትን በሚመለከት ጥቂት ድንጋጌዎችን ይዟል ፡፡ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 1 እንዲህ ይላል፡—

« ማንኛውም የውጭ አገር ሰው ከንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ውጭ ሆኖ <u>በወል ሕግ መብት</u> ላይ ባደረገው ወንጀል የተከሰሰ ወይም የቅጣት ፍርድ የተፈረደበት እንደሆነና ወደ ኢትዮጵያ የገባ እንደሆነ ሕጉ እንደሚያዘው በመንግሥት ውል

1 ነጋሪት ጋዜጣ በተለይ የወጣ ቁጥር 11957 (እ. ኤ. አ.) አዋጅ ቁጥር ፤ 1957 (እ. ኤ. አ.)

ስምምነት በኢንተርናሲዮናል ሕግ መሠረት አጥፊው የሠራው ወንጀል የኢትዮጵያን መንግሥት በቀጥታና በዋና ባለጉዳይነት የማያገባው ሆኖ ሲገኝና ወንጀሉን የሠራበት አገር መንግሥት በግዛቱ ሕግ መሠረት ቅጣቱን እንዲፈጽም አግባብ ያለው ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ተይዞ ቅጣቱን ወደሚፈጽምበት አገር እንዲተላለፍ ሊደረግ ይችላል ። » ( ስርዝ የተጨመረ ) ይህን ድንጋጌ በሚመለከት በመጀመሪያ በግልጽ የሚታየው አሳልፎ ሊሰጥ የሚችለው የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ብቻ መሆኑን ሲሆን ይህ ደግሞ የራስ ዜጋን አሳልፎ መስጠት አይቻልም ከሚለው መሠረተ ሀሳብ ጋር የሚጣጣም ነው ። ሁለተኛው ደግሞ ኢትዮጵያ ወንጀለኞችን አሳልፋ የምትሰጠው ጥያቄው የተመሠረተባቸው ወንጀሎች ፖለቲካው ያልሆኑ ተራ ጉዳዮች ሲሆኑ ብቻ ነው ። በአንድ በተወሰነ ጉዳይ የአንድን ፖለቲካዊ ያልሆነ ወንጀል መለኪያዎች ለመወሰን በአጠቃላይ ከባድ ነገር ነው ። ምንም እንኳ በሕጉ ድንጋጌ በየትኛውም ቦታ ትርጉሙ ያልተሰጠ ቢሆንም በተለይም በጸሐፊዎች ዘንድ ሁለንተናዊ ተቀባይነት ያገኘው ተራ ወንጀል ( ኦርዲናሪ ኦፌንስ ማለት ፖለቲካ ያልሆነ ወንጀል ማለት ነው ) የሚለው ነው ። ምንም እንኳ በዚህ ጥያቄ ላይ ወደ ዝርዝሩ መግባት ከዚህ ጽሑፍ ዓላማ ውጭ ቢሆንም ወንጀለኛው ተመልሶ ይሰጠኝ የሚል ጥያቄ የቀረበበት አንድ ወንጀል ፖለቲካዊ መሆኑን ለመወሰን ቀላል ሥራ እንዳልሆነ መጥቀሱ አስፈላጊ ነው ። በተቃራኒው ደግሞ በማንኛውም አሳልፎ የመስጠት ክርክር ላይ በጣም ከባድ ችግር የሚነሳው ተመልሶ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበበት በጥገኝነት ላይ ያለ ወንጀለኛ ተመልሶ እንዲሰጥ የተጠየቀበት ወንጀል የፖለቲካ ጠባይ ያለው መሆኑን ለመወሰን ብቃት ያለው ወንጀለኛውን አሳልፎ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበለት መንግሥት መሆኑ ነው ። ይህን በሚመለከት የየሀገሩ አሠራር በመሠረተ ሀሳቡ አፈጻጸም ላይ አነስተኛ ነው የማይባል ልዩነት ይታይበታል ፤ ምክንያቱም በሀገሪቱ ሕግ ላይ በመመሥረትና ሁኔታውን በመመርኮዝ አንድ ወንጀል ፖለቲካዊ መሆኑን ለመወሰን ከፍተኛ ሥልጣን የተሰጠው ወንጀለኛውን አሳልፎ እንዲሰጥ ጥያቄ ለቀረበለት መንግሥት የፍርድ ወይም የአስፈጻሚ አካል በመሆኑ ነው ።

ቀጥለን በአንቀጽ 21 ውስጥ ወዳለው ሐረግ እንምጣ ። ይህም ሐረግ « በሕጉ ድንጋጌ መሠረት ፣ በውሎች ወይም በኢንተርናሲዮናል የልማድ ሕግ መሠረት ተይዞ ቅጣቱን ወደሚፈጽምበት አገር እንዲተላለፍ ሊደረግ ይቻላል » ይላል ። በጥገኝነት ላይ ያለውን ወንጀለኛ አሳልፎ ለመስጠት ከእነዚህ አንዳቸውን መጠቀም ይቻላል ።

‘ ውሎች ’ ማለት አሳልፎ የመስጠት ውሎች ወይም አሳልፎ መስጠትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን የያዙ ሌሎች ውሎች ‘የኢንተርናሲዮናል የልማድ ሕግ ’ ማለት ሲሆን ይህ ደግሞ የሚመለከተው የሀገሮችን አሠራር ፣ ወይም የኢንተርናሲዮናል የልማድ ሕግን ነው ፤ ነገር ግን « የሕጉ ድንጋጌዎችን » የሚለው ሐረግ ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ አይደለም ። የትኛው ሕግ ? የወንጀለኛ መቅጫው ሕግ? የወንጀለኛ መቅጫው ሥነ ሥርዓት ሕግ? ወይስ ሌላ ማንኛውም ሕግ ወይስ እስካሁን ድረስ የሌለውን ፤ ነገር ግን ሕግ አርቃቂው ወደ ፊት ሊወጣ ይችላል ብሎ ተስፋ አድርጎ ሊሆን የሚችለውን ልዩ አሳልፎ የመስጠት ሕግ ነው የሚመለከተው ? ጥያቄው የተነሳበት ሐረግ ትርጉም ምንም

ይሁን ምን አንድ በጥገኝነት ላይ ያለ የውጭ አገር ወንጀለኛ ከኢትዮጵያ ተመልሶ ሊሰጥ የሚችለው ከሶስቱ ሥነ ሥርዓቶች በአንዱ መሠረት መሆኑ ግልጽ ነው ። በእርግጥ የአንቀጽ 21 ( ሀ ) ግልጽ ትርጉም ወንጀለኛው ተመልሶ ይሰጠኝ ብሎ ከጠየቀው መንግሥት ጋር የተደረጉ የውል ግዴታዎች ባይኖሩም በኢትዮጵያ አንድ በጥገኝነት ላይ ያለ ወንጀለኛን አሳልፎ መስጠት ይቻላል ማለት ነው ፤ ምክንያቱም በአንቀጽ 21 ( 1 ) መሠረት ምንም እንኳ በኢትዮጵያና ወንጀለኛው ተመልሶ ይሰጠኝ ብሎ በጠየቀው መንግሥት መካከል አሳልፎ የመስጠት ውል ባይኖርም የሕጉ ድንጋጌዎች ፣ ወይም ኢንተርናሲዮናል የልማድ ሕግ የሚሉት ሐረጎች ጥገኛውን ወንጀለኛ አሳልፎ ለመስጠት የሚያስችሉ መሠረቶች ይፈጥራሉ ። ይህ ደግሞ በዓለም አቀፍ መግባባት ከተወሰነው ውጭ ማንም ሰው አሳልፎ አይሰጥም ከሚለውና ትርጉሙም ኢትዮጵያ ጥገኛ ወንጀለኞችን አሳልፋ ለመስጠት ግዴታ ከገባችባቸው አሳልፎ የመስጠት ውል ፣ ወይም ስምምነት ፣ ወይም ሌላ ዓለም አቀፋዊ መግባባት በምንም ከማይተናነሰው መሠረተ ሀሳብ ጋር ሊጋጭ ይችላል ።

አንቀጽ 21 ( 1 ) በተጨማሪ ወንጀሉ በቀጥታና በዋናነት የኢትዮጵያን መንግሥት የሚያገባው ከሆነ አንድ በኢትዮጵያ በጥገኝነት ላይ ያለ ወንጀለኛ ለሌላ መንግሥት ተመልሶ አይሰጥም ይላል ( አንቀጽ 13 ) በሌሎች የወንጀለኛ መቅጫው ሕግ ድንጋጌዎች በተብራራው መሠረት በሀገሪቱ ርዕሰ ብሔርና በሀገሪቱ ደህንነት ወይም አንድነት ፣ በሀገሪቱ ተቋሞች ወይም አስፈላጊ ጥቅሞች ላይ ከወንጀሎች አንዱን በውጭ አገር ፈጽሞ በኢትዮጵያ በጥገኝነት ላይ በሚገኝ በማንኛውም ሰው ላይ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ተፈጻሚነት እንዳለው የወንጀለኛ መቅጫው ሕግ አንቀጽ 13 ያብራራል ። ይህም ማለት የዚህ ዓይነት ማንኛውም ወንጀለኛ ለሌላ አገር አሳልፎ መስጠቱ ይቀርና በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ፣ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ፍርድ ይሰጠዋል ማለት ነው ። ነገር ግን የፈጸመው ወንጀል በቀጥታና በዋናነት ኢትዮጵያን የሚመለከት መሆኑን የሚያውቅ ወይም የሚጠረጥር ሰው በኢትዮጵያ በጥገኝነት ይቀመጣል ብሎ መገመት አዳጋች ይሆናል ።

የወንጀለኛ መቅጫው ሕግ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 2 « ጥፋቱን በፈጸመ ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ዜጋ የነበረ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሕጉ ላይ ተገልጾ የተደነገገ ውሳኔ ከሌለ በስተቀር ለሌላ አገር መንግሥት አሳልፎ አይሰጥም ። አሳልፎ ባልተሰጠም ጊዜ በኢትዮጵያ የዳኝነት ሥልጣንና ሕግ መሠረት ይፈረድበታል ። » በማለት ይገልጻል ( ስርዝ የተጨመረ ) የተሰረዘባቸው ሐረጎች ምን ማለት ናቸው ? አንደኛው « በሕጉ ላይ ተገልጾ የተደነገገ ውሳኔ ከሌለ በስተቀር » የሚለው አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ለሌላ መንግሥት አሳልፎ ሊሰጥ የሚችለው በአሳልፎ የመስጠት ውል ወይም በሌላ ማንኛውም ሕግ መሠረት መሆኑን ያመለክታል ። ሁለተኛው « አሳልፎ ባልተሰጠም ጊዜ » የሚለው ሐረግ ደግሞ አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ አሳልፎ ስለመስጠት በተደረገ ውል ወይም ይህንኑ ጉዳይ በሚመለከት የኢትዮጵያ ሕግ ድንጋጌ መሠረት አሳልፎ ሊሰጥ የሚችልበት ሁኔታ መኖርን በግልጽ ያመለክታል ። በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት አሳልፎ መስጠትን በሚመለከት የአንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ደረጃ ከአንድ የውጭ አገር ዜጋ ደረጃ ከውጤቱ አኳያ ሲነጻጸር ያን ያህል ልዩነት የለውም ።

በሁለቱ መካከል አንድ ብቻ ልዩነት አለ ። ይኸውም አንድ የውጭ አገር ዜጋ በዓለም አቀፍ የልማድ ሕግ መሠረት አሳልፎ ሊሰጥ ሲችል ፣ አንድ ኢትዮጵያዊ ግን በዚህ መሠረት አሳልፎ ሊሰጥ የማይችል መሆኑ ነው ። እዚህ ላይ የወንጀለኛው መቅጫ ሕግ በከፍተኛ ደረጃ ከያዘው የራስ ዜጋዎች አሳልፈው የማይሰጡ መሆናቸውን ከሚገልጸው መሠረተ ሀሳብ ጋር የሚጋጭ ሊሆን ይችላል ።

በመጨረሻም ፣ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 3 « በማናቸውም ጉዳዮች ወንጀሉ አሳልፎ የመስጠትን ጥያቄ ካስነሳ ጥያቄው የሚመረመረው በኢትዮጵያ ሕግ መሠረተ ሀሳቦችና በሥራ ላይ ባሉት የውሎች ድንጋጌዎች መሠረት ነው በማለት ይገልጻል ። በአንቀጽ 21 (1) እንዳየነው የሕጉ ድንጋጌዎች ፣ ውሎች ወይም ዓለም አቀፋዊ የልማድ ሕግ አንድን በጥገኝነት ላይ ያለ ወንጀለኛ አሳልፎ ለመስጠት መሠረቶች እንደሆኑ ተገልጿል ። የዚህ ንዑስ አንቀጽ ዓላማ ምን እንደሆነ ግልጽ አይደለም ። አሳልፎ በመስጠት ጉዳይ ላይ ተጨማሪ የመግለጫ መሠረት መስጠት ነው ወይስ የንዑስ አንቀጽ 1 መሠረተ ሀሳብ ተራ ድጋሚ ነው ? እንዲሁ ከፊት ለፊት ሲመለከቱት ተራ ድጋሚ አይመስልም ። ይልቁንስ ተጨማሪ መሠረተ ሀሳብ የሚያስቀምጥ ይመስላል ። ነገር ግን ይህ ተጨማሪ መሠረተ ሀሳብ አንቀጽ 21 (1) ን ለመጠቀም እንዲቻል በማመቻቸት ፋንታ በእርግጥ አምታች ሁኔታ ይፈጥርበታል ። አምታችነቱ በመጀመሪያ የሚመነጨው « የኢትዮጵያ ሕግ መሠረተ ሀሳቦች » ከሚለው ሐረግ ነው ። የትኞቹ የኢትዮጵያ ሕግ መሠረተ ሀሳቦች ? የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ወይስ የወንጀለኛ መቅጫው የሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረተ ሀሳቦች ? ወይስ ከነአካቴውም የሌለው የኢትዮጵያ አሳልፎ የመስጠት ሕግ መሠረተ ሀሳቦች ? በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው « በሕጉ ድንጋጌዎች » የሚለው በንዑስ አንቀጽ 2 ከተጠቀሰው « የኢትዮጵያ ሕግ መሠረተ ሀሳቦች » ከሚለው ጋር አንድ ዓይነት ይሆን ? ልዩነት ካላቸው የትኛው የበላይነት እንዳለው አልተጠቀመም ። የሁለቱ ሐረጎች ትርጉም ምንም ይሁን ምን ፣ አንድ በጥገኝነት ላይ ያለ ወንጀለኛ « በሕጉ ድንጋጌዎች » መሠረት አሳልፎ ይሰጣል ብንል « በኢትዮጵያ ሕግ መሠረተ ሀሳቦች » ከሚለው ጋር ይፃረራል ። የዚህ ንዑስ አንቀጽ ሁለተኛ ችግር ደግሞ በንዑስ አንቀጽ 1 ውስጥ የሚገኘው ዓለም አቀፍ ልማድ የሚለው ሀሳብ አለመኖር ነው ። በአንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት አንድ በጥገኝነት ላይ ያለ ወንጀለኛ አሳልፎ ሊሰጥ የሚችለው በኢትዮጵያ ሕግ መሠረተ ሀሳቦችና ባሉት ውሎች መሠረት ብቻ ሲሆን በንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ግን በተጨማሪ ‘ በዓለም አቀፍ ልምድ ’ መሠረትም አሳልፎ ሊሰጥ ይችላል ። የበላይነት ያለው የትኛው ድንጋጌ ነው ? ‘ ዓለም አቀፋዊ ልምድ ’ የሚለው ሀሳብ ለምን በንዑስ አንቀጽ 3 ውስጥ እንዳልተጨመረ ግልጽ አይደለም ። በእርግጥ ንዑስ አንቀጽ 3 በሞላ አስፈላጊ ካለመሆኑም በላይ ቀደም ብሎ እንዳየነው በአንጻሩ ተጨባጭ አሳልፎ የመስጠት ጉዳይ ላይ ለምንም ዓላማ የማያገለግለውንና ራሱም ድፍን ያለ ፣ በተግባር ለማዋልም አስቸጋሪ የሆነውን አንቀጽ 21ን በሞላ ተፈጻሚ እንዳይሆን ያደርገዋል ።

## ውሎችና ዓለምአቀፍ ስምምነቶች

አሁን ደግሞ ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸውን አሳልፎ መስጠትን የሚመለከቱ ውሎችና አለምአቀፍ ስምምነቶች እንመለከታለን ። አሳልፎ ስለመስጠት በሁለት አገሮች የተደረጉ ውሎችን በሚመለከት ኢትዮጵያ ያላት የዚህ ዓይነት ውል አንድ ብቻ ነው ። ይኸውም በ1964 ( እ.አ.አ. ) ከሱዳን ጋር ያደረገችው አሳልፎ የመስጠት ውል ነው ። ይህ ውል የተፈረመው ማርች 27 ቀን 1964 ( እ.አ.አ. ) ሲሆን ተግባራዊ የሆነው ደግሞ ከኤፕሪል 16 ቀን 1964 (እ.አ.አ. ) ጀምሮ ነው ። እዚህ ላይ የምንመለከተው የውሉን ዋና ዋና ድንጋጌዎች ሲሆን ፣ ይህም አመለካከት አሳልፎ መስጠት በአለምአቀፍ ሕግ ያለውን መልክ በውሎችና በስምምነቶች ከመረጋገጡ አንጻር ይሆናል ።

ቀደም ብሎ በተጠቀሰው የዚህ ጽሑፍ ክፍል ጠንከር ተደርጐ እንደተገለጸው በአሳልፎ የመስጠት ሕግ እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆነው ሁለገብ መሠረተ ሀሳብ የፖለቲካ ወንጀለኞች ተመልሰው የማይሰጡ መሆናቸው ነው ። የኢትዮ— ሱዳን አሳልፎ የመስጠት ውል አንቀጽ 7 ይህን አስፈላጊ መሠረተ ሀሳብ የሚመለከት ድንጋጌ ይዟል ። በዚህ ውል ድንጋጌ መሠረት ፖለቲካ ነክ የሆኑ ወንጀሎች ጥፋተኛውን አሳልፈው አያስጡም ፣ እንዲሁም ተመልሶ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበበት ሰው ስለእርሱ እጅ መስጠት ጥያቄ የቀረበው በእርግጥ ይህን ሰው የፖለቲካ ባህሪ ባለው ወንጀል ወይም ጥፋት ላይ ለመዳኘት ወይም ለመቅጣት ካለ አመለካከት መሆኑን ጥፋተኛው ካረጋገጠ ለጠያቂው መንግሥት ተመልሶ አይሰጥም ። ምንም እንኳ አሳልፎ የመስጠቱ ጥያቄ የቀረበበትን ጥፋት ፖለቲካዊነት የሚወስነው ማን እንደሆነ በዚህ አንቀጽም ሆነ በየትኛውም የውሉ ክፍል ያልተጠቆመ ቢሆንም ውሳኔው መተው ያለበት አሳልፎ የመስጠቱ ጥያቄ ለቀረበለት መንግሥት መሆን ይገባዋል ፤ ምክንያቱም አሳልፎ የመስጠትን ጉዳይ በሚመለከት የመንግሥታት አጠቃላይ የአሠራር ልምድ የዚህ ዓይነት ነውና ። በሁሉም አሳልፎ የመስጠት ውሎችና ስምምነቶች ውስጥ የለም ማለት እንደሚቻለው ሁሉ በዚህ ውልም የፖለቲካ ባህሪ ያለው ጥፋት ምን ምን እንደሚያጠቃልል ለመግለጽ ምንም ሙከራ አልተደረገም ። የዚህ ውል አንዱ ቀላል ነው የማይባል ተጨማሪ ድክመት ደግሞ የውጭ አገር መንግሥትን ርዕሰ ብሔር ፣ ወይም የመስተዳድር መሪ ፣ ወይም ከቤተሰቦቹ አንዱን መግደል አሳልፎ መስጠትን በሚመለከት እንደፖለቲካ ወንጀል መቆጠር እንደሌለበት የሚገልጸው አቴንታንት ክሎዝ የሚባለው በውስጡ አለመኖር ነው ። ይህ ክሎዝ አብዛኛውን ጊዜ በዘመናዊ አሳልፎ የመስጠት ውሎች ወይም ስምምነቶች ውስጥ ተጨምሮ ይገኛል ።

ሌላው ጠቃሚ ሁለገብ መሠረተ ሀሳብ አሳልፎ የመስጠቱ ጥያቄ የተመሠረተበት ጥፋት በሁለቱም ጥያቄውን ባቀረበው መንግሥትና ጥያቄው በቀረበለት መንግሥት ሕጐች የሚያስቀጣ ሆኖ የሚገኝበት ጥምር ወንጀለኝነት ( ዳብል ክሪሚናሊቲ ) የሚባለው ነው ። ይኸው በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የተደረገው ውል በአንቀጽ 2 አሳልፎ የሚያስጡትን ወንጀሎች ከዘረዘረ በኋላ ይህንኑ የሚመለከት ሌላ ተጨማሪና አስፈላጊ ድንጋጌ አስፍሯል ፣ ይኸውም አሳልፎ መስጠቱ ሊከናወን የሚችለው የተዘረዘሩት ወንጀሎች ወይም በመሠረቱ ከነዚህ ወንጀሎች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ጥፋቶች በሁለቱም አገሮች የየግል የአስተዳደር ክልል ቢፈጸሙ ኖሮ በሁለቱም ሕጐች የሚያስቀጡ ጥፋቶች ሲሆኑ ብቻ መሆኑን ይገልጻል ።

ሌላው በሁለቱም አሳልፎ የመስጠት ውሎችና ስምምነቶች ውስጥ ሰፍኖ የሚገኘው ሁለገብ መሠረተ ሀሳብ ደንቡ የሚያገለግለው ለአንድ ጥያቄው ለቀረበበት ጉዳይ ብቻ መሆኑን የሚገልጸው ዘሩል ኦፍ ስፐሻሊቲ የሚባለው ነው ። የኢትዮ—ሱዳን ውል አንቀጽ 5 ( 1 ) ተመልሶ የተሰጠው ሰው እንዲሰጥ ካደረጉት ወንጀሎች ወይም ጥፋቶች በስተቀር በሌሎች ወንጀሎች ወይም ጥፋቶች ወይም በሌላ በማናቸውም ተመልሶ ከመሰጠቱ በፊት ለተፈጸሙ ጉዳዮች አሳልፎ ወደሰጠው አገር እስኪመለስ ወይም ተመልሶ የመሄድ እድል እስኪያገኝ ድረስ ተመልሶ በተሰጠው መንግሥት ክልል እንዲቆይ ወይም ለፍርድ እንዲቀርብ አይደረግም በማለት በተጨማሪ ይደነግጋል ።

ሕገ መንግሥቶቻቸውንና የየሀገሮቻቸውን ሕጎች በማክበር መንግሥታት በአብዛኛዎቹ አሳልፎ የመስጠት ውሎችና ስምምነቶች የራሳቸውን ዜጎች አሳልፈው ላለመስጠት ያላቸውን መብት ይጠብቃሉ ። ይህም በውሉ አንቀጽ 3 « በምንም ጉዳይ ወይም በሆነው ዓይነት ሁኔታ ተዋዋይ ወገኖች ዜጎቻቸውን አሳልፈው ለመስጠት አይገደዱም » በማለት ተደንግጓል ። ኢትዮጵያን በሚመለከት ይህ ድንጋጌ የኢትዮጵያን ዜጋ ለሌላ መንግሥት አሳልፎ መስጠትን የሚከለክለውን የታገደውን ሕገ መንግሥት አንቀጽ 50 የሚጠብቅ ነበር ፤ ነገር ግን ‘ ተገዳጅ ስላለመሆን ’ ከሚጠቅሰው ሐረግ አኳያ ሲታይ የውሉ አንቀጽ 3 እንዳደፍ የሚጠቁመው ተዋዋይ ወገኖች ከፈለጉ የየራሳቸውን ዜጋዎች ለሌላው መንግሥት አሳልፈው መስጠት እንደሚችሉ ነው ። ይህም ማለት አሳልፎ ይሰጠኝ የሚል ጥያቄ በሱዳን መንግሥት በኩል ቀርቦበት በኢትዮጵያ መንግሥት ጥያቄው ተቀባይነት ያገኘ የኢትዮጵያ ዜጋ ውሳኔውን ለመቃወም የውሉን አንቀጽ 3 በማንሳት ተከራክሮ ከውሳኔው ማምለጥ አይችልም ማለት ነው ። ስለዚህም ይህን የሚጻረር ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ከሌለ በውሉ መሠረት በመሠረተ ሀሳብ የኢትዮጵያ ዜጋ አሳልፎ ለመስጠት የተጋለጠ ሊሆን ይችላል ። ይሁን እንጂ ወደፊት ይህ ሁኔታ መፈጠሩ አጠራጣሪ ነው ። ምክንያቱም ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ረቂቅ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 32 ማንም ኢትዮጵያዊ ለሌላ አገር ተላልፎ እንደማይሰጥ በግልጽ ያስቀመጠ በመሆኑ ነው ። ከዚህ ሌላ የረቂቁ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34/2 ዜግነት የሌላቸው ሰዎችም ቢሆኑ ከኢንተርናሽናል ስምምነት ውጭ ለሌላ አገር ተላልፈው እንደማይሰጡ የሚደነግግ በመሆኑ ከቀድሞው ሕገ መንግሥት የተሻለ ጥበቃ ያደርጋል ።

የውሉ አንቀጽ 13 ደግሞ የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማስፈር ለጥገኛው ወንጀለኛ ጠቃሚ መከላከል ያደርግለታል ፤ ይኸውም 1/ ጥገኛው ወንጀለኛ እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በስልሳ ቀናት ውስጥ ወይም ጥያቄውን ያቀረበው መንግሥት ፍ/ቤት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ከዚህ ሊበልጥ በሚችለው የጊዜ ገደብ ውስጥ አሳልፎ ለመስጠት የሚያስችል በቂ ማስረጃ ካላቀረበ ጥገኛው ወንጀለኛ በነጻ መለቀቅ አለበት ። 2/ በውሉ መሠረት ጥገኛው ወንጀለኛ ተመልሶ መሰጠት አለበት ተብሎ በፍ/ቤት ከተወሰነበት በኋላ ከውሳኔው ቀን ጀምሮ ባሉት ሰላሳ ቀናት ውስጥ አሳልፎ ከሰጠው መንግሥት የአስተዳደር ክልል ተነስቶ ካልተወሰደ በነጻ ሊለቀቅ ይችላል ይላል ። እዚህ ላይ ሊታወስ የሚገባው በቁጥር አንድ በተጠቀሰው መሠረት የተወሰነው የጊዜ ገደብ ካለፈ የጥገኛው ወንጀለኛ በነጻ መለቀቅ ግዴታ ሲሆን በቁጥር ሁለት መሠረት ግን እንደ አማራጭ ሆኖ በመቅረቡ የጥገኛው ወንጀለኛ በነጻ መለቀቅ አሳልፎ የመስጠቱ ጥያቄ ለቀረበለት መንግሥት ርህራሄ ተትቷል ። እንደዚህ ባለው ሁኔታ በነጻ ያልተለቀቀ ጥገኛ ወንጀለኛ ያለው መፍትሄ ከሕግ ውጭ ታስሬአለሁ በማለት

ጉዳዩ በፍ/ቤት እንዲታይለት ማመልከት ብቻ ነው ። በውሉ ውስጥ ልዩ የሆነ ድንጋጌ ያለው አንቀጽ 6 ነው ። ይህም አንቀጽ ወንጀለኛው ተመልሶ ይሰጠኝ የሚለው ጥያቄ ጥፋተኛው ሕግን በመጣሱ ብቻ ( ኢን ኮንቱማሺያም ) በመመሥረት በተሰጠ ፍርድ ላይ የተመረኮዘ መሆን እንደሌለበት ይገልጻል ። የዚህም ድንጋጌ ዓላማ በሌለበት ጉዳዩ በፍ/ቤት የታየውንና የተፈረደበትን ሰው መብት ለመከላከል መሆኑ ግልጽ ነው ፤ ምክንያቱም ጉዳዩ በፍ/ቤት ሲታይ ቀርቦ እንዳልተከራከረ እሙን ሆኖ ሳለ ይህን ሰው አሳልፎ መስጠት በደልና የሕግ መብቱን በመንፈግ ( ዊዛውት ዱ ፕሮሰስ ኦፍ ሎ ) ነጻነቱን የመከልከል ያህል ነው ። ይህ የውሉ ድንጋጌ ተመልሶ ይሰጠኝ ብሎ ጠያቂው መንግሥት የተወነጀለው ሰው በሌለበት ጉዳዩን ካየና ፍርድ ከሰጠ በኋላ ፍርዱን በሀገሩ ውስጥ ለመፈጸም ወንጀለኛው ይሰጠኝ ብሎ ከመጠየቅ ያግደዋል ። እንደዚህ ያለ ድንጋጌ ከሌለ ጠያቂው መንግሥት የተወነጀለው ሰው በሌለበት ጉዳዩን ለማየት ይገፋበታል ፤ ምክንያቱም ሰውየው ጥፋተኛ ነው ብሎ ለመወሰን በዚህ መንገድ መጠቀሙ ሰውየው ባለበት ከመወሰን አንጻር ቀላል ሆኖ ስለሚያገኘው ነው ። ክፋቱ የዚህ ዓይነት ድንጋጌ ሰፍሮ የሚገኘው እጅግ በጣም ጥቂት በሆኑ አሳልፎ የመስጠት ውል ወይም ስምምነቶች ውስጥ ነው ።

እጅግ በጣም ጥቂቶች አይኖራቸው እንደሁ እንጅ ሁሉም አሳልፎ የመስጠት ውሎችና ስምምነቶች ጥገኛውን ወንጀለኛ አሳልፎ ለመስጠት በመጀመሪያ በሰውየው ላይ የሞት ቅጣት የማይፈጸምበት መሆኑን ፥ ወይም የሞት ቅጣት ተፈርዶበትም ከሆነ ወደ ዝቅተኛ ቅጣት የሚቀነስበትን ሁኔታ መነሻ የሚያደርጉ ድንጋጌዎችን ይይዛሉ ። ይሁን እንጅ እየተመለከትነው ያለነው በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የተደረገው ውል የዚህ ዓይነት ድንጋጌ የለውም ፤ ስለዚህም ጠቃሚና ሁለገብ የሆኑት የዘመናዊ አሳልፎ የመስጠት ሕግና አሠራር መሠረተ ሀሳቦች ይጐድሉታል ።

እንደ ደንብ ሆኖ ለሀገር ውስጥ አሳልፎ የመስጠት ሕጎች የተተወውን አሳልፎ የመስጠት ሥነ ሥርዓት በሚመለከት የውሉ አንቀጽ 8 ጥፋተኛው ተመልሶ ይሰጠኝ ተብሎ የሚቀርበው ጥያቄ በጠያቂው መንግሥት ፍ/ቤት በተጻፈ የመያዣ አባሪነት መቅረብ የሚገባው መሆኑን ፥ ወይም ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠ ሰውን በሚመለከት ይኸው ጥያቄ ጥፋተኛነቱ በተወሰነበት ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት አባሪነት መቅረቡን አስፈላጊ ያደርገዋል ። እነዚህ ሥነ ሥርዓቶች ከተሟሉ በኋላ ብቻ ነው ጥያቄው የቀረበለት መንግሥት በጥገኝነት ላይ የሚገኘውን ወንጀለኛ በቁጥጥር ስር ለማድረግ በአንቀጽ 7 መሠረት የሚቀጥለው ።

በውሉ አንቀጽ 10 መሠረት አሳልፎ መስጠቱ ሊፈጸም የሚችለው ሰውየው የተከሰሰበት ወንጀል ወይም ጥፋት ጥያቄው በቀረበለት መንግሥት የአስተዳደር ክልል ቢፈጸም ኖሮ የቀረበው ማስረጃ በዚሁ አገር ሕጎች መሠረት እስረኛውን ለፍርድ ለማቅረብ ትክክል መሆኑን ለማሳመን ፤ ወይም እስረኛው ተመልሶ ይሰጠኝ ብሎ ጥያቄውን ባቀረበው ተዋዋይ መንግሥት ፍ/ቤቶች ጥፋተኛ ነው ተብሎ የተወሰነበት ሰው መሆኑን ለማረጋገጥ በቂ ሆኖ ሲገኝ ነው ። ይኸው አንቀጽ ተመልሶ መስጠቱን እንዲጠባበቅ በእስር ላይ ያለ ማንኛውም ወንጀለኛ ለእስር ከተዳረገበት ቀን ጀምሮ አስራ አምስት ቀናት እስኪያልፉ ተመልሶ ሊሰጥ እንደማይችል በተጨማሪ ይገልጻል ። እዚህ ላይ መታወስ ያለበት 1/ የጥገኛው ጥፋተኝነት በማያጠራጥር ሁኔታ መረጋገጥ የግድ አይደለም 2/ እስረኛውን ለፍርድ ማቅረብ ትክክለኛ መሆኑን ለማሳመን የሚችል ማስረጃ ማቅረቡ በቂ ነው ። 3/ ጥገኝነት የጠየቀው ሰው ተመልሶ ከመሰጠቱ

በፊት ከታሰረበት ቀን ጀምሮ አስራ አምስት ቀናት ማለፍ አለባቸው ። የሶስተኛው ጉዳይ አስፈላጊነት በጥገኝነት ላይ ያለው ሰው ያለአግባብና ከሕግ ውጭ ታሰርኩ ብሎ ለፍ/ቤት ለማመልከት ጊዜ እንዲያገኝ ለማድረግ ነው ብሎ ለመቀበል አያዳግትም ።

ጥፋተኛው ተመልሶ ይሰጠኝ በሚለው ጥያቄ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ጉዳዩ ፍ/ቤት ቀርቦ መሰማት ያለበት መሆኑን ይህ ውል ዘርዝሮ አያስረዳም ። ይሁን እንጂ ጥያቄው የቀረበለት መንግሥት ባለሥልጣኖች በውሉ አንቀጽ መሠረት ‘ መመርመር ’ ስለሚገባቸው ሁኔታዎች አንቀጽ 11 ደንግጓል ። እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ‘ ምርመራ ’ ማለት ጉዳዩን መስማት ከሚለው ጋር ተመሳሳይ መሆን አለመሆኑ ግልጽ አይደለም ። ይሁን እንጂ « ምርመራ » የሚለው ቃል ለተፈላጊው ሰው የመሰማት እድል ለመስጠት እንደሆነ ተቆጥሮ ካልተተረጎመ የአስራ አምስቱ ቀን ማለፍ ድንጋጌ ጠቃሚነቱ አይታይም ።

በዚህ ጸሐፊ አስተሳሰብ ሁለቱም ተመሳሳይ ናቸው ፤ ምክንያቱም አንቀጽ 11 ( 1 ) ተመልሶ ይሰጠኝ ብሎ በጠየቀው መንግሥት ክልል ውስጥ በመሀላ የተሰጠን የምስክርነት ቃል ወይም ምስክሮች ያረጋገጡትን በሚመለከት ትክክለኝነቱ የተረጋገጠ ከሆነ ለመረጃነት ተቀባይነት እንዳለው ይገልጻል ፤ ወይም የምስክርነቱን ቃል ቅጅ እንደዚሁም በፍ/ቤቱ የተሰጡትን የእስራት ትዕዛዝና ውሳኔዎች ፥ ወይም ቅጃቸውን ፥ የጽሑፍ ማስረጃዎችን ፥ ወይም የሰውየው ወንጀለኝነት የተረጋገጠባቸውን የፍ/ቤት መዛግብት ለመረጃነት ተቀባይነት እንዳላቸው ይደነግጋል ። ይህ የተብራራ ድንጋጌ በግልጽ የሚያሳየን በጥገኝነት ላይ ያለው ወንጀለኛ ተመልሶ ከመሰጠት ለመዳን በሆነ መድረክ ሁሉንም የሚቻለውን የመከላከል ወይም የተቃውሞ ክርክር ለማቅረብ እድል ሊሰጠው እንደሚገባ ነው ።

ለማጠቃለል ፦ በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የተደረገው አሳልፎ የመስጠት ውል ቀደም ብሎ በተሰጠው ማብራሪያ እንደተጠቀሰው ካሉት ጥቂት ድክመቶች በስተቀር እጅግ በጣም ጥቂቶች ይቀሩ እንደሁ እንጂ ሁሉንም ጠቃሚና ሁለገብ አሳልፎ የመስጠት መርሆዎች ስለሚይዝ ዓይነተኛ አሳልፎ የመስጠት ውሎችን ወይም የሀገር ውስጥ አሳልፎ የመስጠት ሥነ ሥርዓት ሕግ ለመንደፍ እንደ ናሙና ሊያገለግል ይችላል ።

## ዓለምአቀፍ ስምምነቶች

በዚህ ርዕስ ሥር ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸውን በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተደረጉና አሳልፎ ስለመስጠት ድንጋጌዎችን የያዙ አራት ስምምነቶችን እንመረምራለን ።

### 1. የሰው ዘርን በመደዳ የመፍጀት ወንጀልን ስለመቆጣጠርና ስለቅጣቱ በ1948 ( እ.አ.አ. ) የተደረገ ስምምነት [2]

ይህ ስምምነት የተደረገው በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ስብሰባ ዲሰምበር 9 ቀን 1948 ( እ.አ.አ. ) ነበር ። ኢትዮጵያም ስምምነቱን ጁላይ 1 ቀን 1949 ( እ.አ.አ.) አጽድቃዋለች ። ከዲሰምበር 31 ቀን 1982 ( እ.አ.አ. ) ጀምሮ

2 UNTS Vol. 78 ፤ ገጽ 277

87 አገሮች የስምምነቱ አባላት ናቸው ። የዚህ ስምምነት አንቀጽ 8 የሰው ልጆ ችን በመደዳ መፍጀትንና ሌሎች በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን ተግባሮች ፤ ይኸ ውም በሰዎች ላይ እልቂት ለመፈጸም ማሴር ፣ በሰዎች ላይ እልቂት እንዲፈጸም በቀጥተኛ መንገድ ሕዝብን ማነሳሳት ፣ እልቂት ሲፈጸም መተባበር አሳልፎ ለመስጠት ዓላማ እንደፖለቲካ ወንጀሎች እንደማይቆጠሩ ይገልጻል ። ተዋዋይ ወገኖች እንደዚህ ባሉ ጉዳዮች በሕጎቻቸውና በሥራ ላይ ባሉ ውሎች መሠረት አሳልፈው ለመስጠት ቃል ገብተዋል ። ይህን ድንጋጌ በአንድ የተለየ ጉዳይ ላይ ስናውለው ከላይ የተመለከትናቸው እውቅ መሠረተ ሀሳቦች በእርግጥም ያገለግላሉ ።[4]

## 2. ስለ አደንዛዥ እጾች በ1961 (እ.አ.አ.) የተደረገ ስምምነት[3]

ኢትዮጵያ የዚህ ስምምነት አባል የሆነችው አፕሪል 29 ቀን 1965 (እ.አ.አ) ነበር ። የስምምነቱ አንቀጽ 30 (ለ) በክፍል 1 እና 2 (ሀ) 11/ መትከል ፣ ማምረት ሥርቶ ማውጣት ፣ መሸጥ ፣ ማስተላለፍ ፣ መደለል ፣ መላክ ወዘተ ተብ ለው በተጠቀሱት የአደንዛዥ እጾች አሻጥር እና ሙከራ ጥፋቶች አሳልፈው እን ደሚያሰጡ ወንጀሎች ሆነው በማናቸውም ከአሁን በፊት በተደረጉም ሆነ በማንኛቸውም ተዋዋይ መካከል ወደፊት በሚደረጉ አሳልፎ የመስጠት ውሎች ውስጥ አሳልፈው እንደሚያሰጡ ወንጀሎች ሆነው መግባታቸው አስፈላጊ መሆ ኑን ፣ እንዲሁም የውሎችንና የጋራ ስምምነቶችን መኖር አሳልፎ ለመስጠት እንደ መነሻ ነጥብ አድርገው በማይቆጥሩ ተዋዋይ ወገኖች መካከል አሳልፈው እንደ ሚያሰጡ ወንጀሎች ሆነው መቆጠር እንዳለባቸው ይደነግጋል ። ይህም አሳ ልፎ መስጠት ሊፈጸም የሚችለው ጥያቄው ከቀረበለት ተዋዋይ መንግሥት ሕግ ጋር በተጣጣመ መልክ መሆን አለበት ። ከዚህም ሌላ ጥያቄው የቀረበ ለት ወገን ባለሥልጣኖች ጥፋቱ አደገኛ ነው ተብሎ ሊቆጠር የሚበቃ አይደለም ካሉ ወንጀለኛው እንዲታሠር ወይም አሳልፎ እንዲሰጥ የቀረበውን ጥያቄ ላለ መቀበል መብት ይኖራቸዋል ይላል ። ከዚህ ጋር በማያያዝ ሊታወስ የሚገባው በኢትዮጵያና የዚሁ ስለአደንዛዥ እጾች የተደረገው ስምምነት አባል በሆነ ችው ሱዳን መካከል የተደረገው አሳልፎ የመስጠት ውል ከአደንዛዥ እጾች ጋር የተያያዙ ጥፋቶች አሳልፈው ከሚያሰጡት ወንጀሎች መካከል መሆናቸውን ጭምር መያዙ ነው ።[4]

## 3. በመብረር ላይ ባለ አውሮፕላን ላይ ስለሚፈጸሙ ጥፋቶችና ሌሎች ተግባ ሮች የተደረገ ስምምነት (ቶኪዮ ፣ /እ.አ.አ./ሴፕተምበር 14 ቀን1965[5]

ይህ ስምምነት በዓለምአቀፍ ሲቪል አቪየሽን ድርጅት እርዳታና ድጋፍ ከተ ደረጉት ከአየር ትራንስፖርት ደህንነት ጋር የተያያዙ ተከታታይ ውሎች የመ ጀመሪያው ነበር ። ውሉም የጸናው ዲሰምበር 4 ቀን 1967 ነው ። ከአገስት ወር 1983 (እ.አ.አ.) ጀምሮ 112 አገሮች የስምምነቱ አባላት ነበሩ ። ኢትዮጵያ ውሉን ያጸደቀችው ማርች 27 ቀን 1977 (እ.አ.አ.) ነው ።

---

[3] 118 UNTS 52 ፤ ገጽ 252

[4] አንቀጽ 4 ፤ ፓራግራፍ 22

[5] UNTS Vol. 704 ፤ ገጽ 219

ስምምነቱ ስለአውሮፕላኑ አዛዥ ሥልጣንና አውሮፕላኑ በሕገወጥ መን ገድ በሚያዝበት ወቅት የስምምነቱ አባል አገሮች ስለሚወስዷቸው እርምጃዎች ደንግጓል ። ምንም እንኳ ስምምነቱ አሳልፎ መስጠትን ግዴታ ባያደርገውም በአንድ የውሉ አባል አገር አውሮፕላን ላይ የተደረጉ ጥቃቶች አሳልፎ ለመስ ጠት ዓላማ ሲባል ድርጊቱ በተፈጸመበት ቦታ ብቻ ሳይሆን አውሮፕላኑ በተ መዘገበበት አገር ክልል ውስጥም ጭምር እንደተፈጸሙ መቆጠር አለባቸው በማ ለት በአንቀጽ 16(1) ደንግጓል ።

## 4. የአውሮፕላንን በሕገወጥ መንገድ መያዝ ስለመከላከል የተደረገ ስምምነት (ሄግ ፣ /እ.አ.አ./ ዲሰምበር 16 ቀን 1970/[6]

ይህ ስምምነት ዋና ጉዳይ አድርጎ የሚያነሳው ስለ አውሮፕላን ጠለፋ ሲሆን ይህም በቶኪዮ ስምምነት ላይ ማሻሻያ እንዲሆን የተደረገ ነው ። ከአገስት ወር 1983 (እ.አ.አ.) ጀምሮ 117 አገሮች የስምምነቱ አባላት ናቸው ። ኢትዮጵ ያም ማርች 26 ቀን 1977 (እ.አ.አ.) የዚህ ስምምነት አባል ሆናለች ። የስም ምነቱ አንቀጽ 7 እና አንቀጽ 8 አሳልፎ መስጠትን የሚመለከቱ ናቸው ። አን ቀጽ 7 ለተዋዋይ መንግሥታት አጥፊውን ለፍርድ የማቅረብ ወይም አሳልፎ የመ ስጠት ምርጫ ይሰጣቸዋል ። ለዚህም የሚከተለውን ደንግጓል ።

> ጥፋተኛ ነው የተባለው ሰው በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ተዋዋይ መንግ ሥት ሰውየውን አሳልፎ ካልሰጠ ያለምንም የሆነው ዓይነት ልዩነት ፣ ጥፋቱ በክልሉ ውስጥ የተፈጸመም ሆነ አልሆነ አሳልፎ ለመስጠት ዓላማ ሲባል ጉዳዩን ብቁ የሆኑ የራሱ ባለሥልጣኖች እንዲያዩት እን ዲያቀርብ ይገደዳል ።

በአንቀጽ 8 ክፍል አንድ መሠረት ጥፋቱ በስምምነቱ አባል መንግሥታት መካከል ባለ አሳልፎ የመስጠት ውል ውስጥ አሳልፎ የሚያሰጥ ጥፋት ነው ተብሎ እንደገባ መቆጠር እንዳለበት ተደንግጓል ። በተጨማሪም ማንኛውም ተዋዋይ መንግሥት በራሱ ሕግጋት መሠረት አሳልፎ የመስጠትን መነሻ ሁኔታ የው ልን መኖር የሚያደርግ ከሆነ አሳልፎ ስለመስጠት ጥያቄ በቀረበለት ወቅት በራሱ ምርጫ ስምምነቱን አሳልፎ ለመስጠት ሕጋዊ መሠረት ለማድረግ እንደ ሚችል ተደንግጓል ። ይሁን እንጅ አሳልፎ የመስጠት ተግባር ጥያቄው በቀረ በለት ወቅት በራሱ ምርጫ ስምምነቱን አሳልፎ ለመስጠት ተግባር ጥያቄው በቀረበለት መንግሥት ሕግ በተሰጡት ሌሎች መነሻ ሁኔታዎችም ተገዥ መሆን እንዳለበት ተተንትኗል ። በአንቀጽ 8 ክፍል ሶስት መሠረት የውልን መኖር አሳልፎ ለመስጠት መነሻ ሁኔታ የማያደርጉ ተዋዋይ መንግሥታት ጥፋ ቱን በነሱ መካከል አሳልፎ እንደሚያሰጥ ጥፋት ለመቁጠር ይገደዳሉ ፤ ይሁን እንጅ ጥፋቱን አሳልፎ እንደሚያሰጥ የመቁጠሩ ሁኔታ ጥያቄው በቀረበለት መንግሥት ሕግ በተሰጡት የመነሻ ሁኔታዎች የሚገዛ ይሆናል ።

---

[6] 10 ኢንተርናሽናል ሌጋል ማተሪያልስ (1971) ፣ ፒጅ 133.

5. በሲቪል አቬሽን ላይ የሚደረገውን የአመጽ ተግባር ለማዳከም የተደረገ ስምምነት[7]/ሞንትሪያል፤/እ.አ.አ./ሴብቴምበር23 ቀን1971/

ይህ ስምምነት የሚመለከተው በአገልግሎት ላይ ያለን አውሮፕላን ከጥቅም ውጭእንደማድረግ፡ወይም እንደማበላሸት፡ወይም እንደየአየር ጉዞ አሙች ሁኔታዎችን ከጥቅም ውጭ ማድረግ ካሉት የአውሮፕላን ጠለፋ ተግባሮች ሌላ በአውሮፕላኖችና በአየር ትራንስፖርት ላይ የሚደረጉትን ሕገወጥ ተግባሮች ነው።/እ.አ.አ./ ከኦገስት ወር1983 ጀምሮ117 አገሮች የስምምነቱ አባላት ናቸው።ኢትዮጵያ ስምምነቱን የተቀበለችው (እ.አ.አ.) ማርች 26 ቀን 1977 ዓ.ም. ነበር ።

ይህ ስምምነት አሳልፎ መስጠትን በሚመለከት በአንቀጽ7 እና8 የያዘው ከላይ ከጠቀስነው ከሄግ ስምምነት ጋር አንድ ዓይነት የሆኑ ድንጋጌዎችን ነው ።እነዚህም ድንጋጌዎች ተዋዋይ መንግሥታት የወንጀለኛውን ጉዳይ ራሳቸው በዳኝነት የማየት ወይም ሰውየውን አሳልፈው የመስጠት ምርጫ ማድረግ እንደሚችሉ፤ በስምምነቱ የተዘረዘሩትን ጥፋቶች አባል መንግሥታት በሚያደርጉዋቸው አሳልፎ የመስጠት ውሎች አሳልፈው የሚያስጡ አድርገው እንዲቆጥሩዋቸው፤ በስምምነቱ የተጠቀሱትን ጥፋቶች አባል መንግሥታት ወደፊት በመካከላቸው በሚያደርጉዋቸው ውሎች አሳልፈው የሚያስጡ ናቸው ብለው ለመጨመር ግዴታ የገቡትን በሚመለከት የተዘረዘሩት ናቸው ሕጎቻቸው አሳልፎ መስጠት የሚመሠረተው በውል መኖር እንደሆነ አድርገው የማይቆጥሩ አገሮች ስምምነቱሊገታቸው የሚያስባቸውን ወንጀሎች ጥያቄ የቀረበለትን መንግሥት አሳልፎ የመስጠት ሕጎችና ደንቦች በማይቃረን ሁኔታ አሳልፈው እንደሚያስጡ አድርገው በመካከላቸው ለመቀበል ግዴታ ገብተዋል ።

## መደምደሚያ

ይህ ጽሑፍ አሳልፎ መስጠትን በሚመለከት የኢትዮጵያ ሕግ በአሁኑ ወቅት ያለበትን ሁኔታ ለመተንተን ሞክሯል ። ከውሎችና ከስምምነቶች በስተቀር የኢትዮጵያ የራሷ አሳልፎ የመስጠት ሕግ ጎደሎና አምታች በመሆኑ በአንድ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተግባራዊ ሆኖ ምንም ያህል ጠቃሚ አገልግሎት እንደማይሰጥ አይተናል ። ይህም ድክመት በተለይ በወንጀለኛ መቅጫው ሕግ ስለአሳልፎ መስጠት የተደነገጉትን እንዳየነው እውነት ነው ። ስለዚህም የተሟላ አሳልፎ የመስጠት የሀገር ውስጥ ሕግ አስፈላጊነት የጎላ ነው ። ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች ጋር የተደረጉ ብዙ አሳልፎ የመስጠት ውሎች ስለሌሏትና የውል ግዴታዎች በሌለበት አሳልፉ የመስጠት ልምድም ስለማትከተል የሀገር ውስጥ አሳልፎ የመስጠት ሕግ መኖር አስፈላጊ አይደለም የሚል ክርክር ሊነሳ ይችላል ። ነገር ግን የዚህ ክርክር መልስ ቀላል ነው፤ ይኸውም ከላይ ያነሳናቸው በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የተደረገው ውልና ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ኢንተርናሽናል ስምምነቶችም እንኳ ብሔራዊ አሳልፎ የመስጠት ሕግ እንዳለ መቁጠራቸው ነው ። በተጨማሪም ኢትዮጵያ ወደፊት ሌሎች አሳልፎ የመስጠት ውሎች ከሌሎች መንግሥታት ልትዋዋል ወይም ለሎች ተጨማሪ ኢንተርናሽናል ስምምነቶች አባል ልትሆን ስለምትችል እነዚህን የምትፈጽምበት መሠረት ያስፈልጋታል።መንግሥታት አባል የሆኑባቸው ስለአሳልፎ መስጠት የሚደረጉ ውሎችና ስምምነቶች መልክ ያለው አፈጻጸም እንዲኖራቸው ምንጊዜም የሀገር ውስጥ አሳልፎ የመስጠት ሕግ ያስፈልጋቸዋል ። ባለፉት አመታት ስለአሳልፎ መስጠት የቀረቡትን በጣም ጥቂት ጥያቄዎች ለመፍታት የመንግሥት ባለሥልጣኖችን ያጋጠሙዋቸው ችግሮች አሳልፎ የመስጠት ደንቦችና ሥነ ሥርዓቶች እንደሚያስፈልጉ በግልጽ አሳይተዋል።ኢትዮጵያ አሳልፎ መስጠትን የሚመለከት አንድ ወጥሕግ ካወጣችየወንጀለኛ መቅጫውድን ጋጌዎች በአዲሱ ሕግ ድንጋጌዎች ይተካሉ ።

[7] 10 ኢንተርናሽናል ሊጋል ማተሪያልስ (1971 ፤ ፣ ገጽ1151.